# ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ




*"ሊፈርስ ያለ ከተማ ፣ ነጋሪት ቢጎሰም አይሰማ"* ይላሉ አበው ሲተርቱ ። ይህ አባባል በውነት ዛሬ በሐገራችን በተለይ በአማራው ላይ እየተተገበረ ያለ አባባል ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ አይሆንም ።

ምናልባት ዛሬ በአማራው ላይ የተጋረጠው አደጋ ላልተገነዘቡትና የአማራውን መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ለማያውቁ ካርታውን ባልቀበለውም የትግሬው ወያኔ በከለለው መሰረት አማራው አለምንም ማፈግፈጊያ እንዴት አጣብቂኝ ውስጥ እንደገባ የሚያመላክት ስዕላዊ ማስረጃ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ ።

ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ፣ አክቲቪስቶች ፣ ጸሀፊዎች ፣ ሐገር ወዳዶች በሐገራችን ያለውን በጎጥ የተቃኘ አደገኛ የሆነ የፖለቲካ አካሄድ ለዘመናት ሲያወግዙ እንደቆዩ ይታወቃል ። በተለይ የትግሬ ወያኔዎች አገዛዝ ከወደቀ ወዲህ ምናልባት ሐገራችን ወደተሻለ የፖለቲካ ስርዐት በመግባት ለሐገርና ለወገን የሚበጅ አስተዳደር ይመሰረታል የሚል ተስፋ ባብዛኛው ሐገር ወዳድ ተጸንሶ ነበር ፣ ሆኖም ግን በተረኝነት መንፈስ የመጣው ሌላው ጠባብ የኦሮሞ ኦነጋውያን ቡድን ከትግሬው ወያኔ በከፋ በኬኛና በግንጠላ መንፈስ የተጠመቀና የተቃኘ በመሆኑ የሐገራችንን ውድቀት እያፋጠነ ይብሱንም ከድጡ ወደማጡ እየጎተታት እንደሆነ የማንክደው ሃቅ ከሆነ ይኸው ሁለተኛ ዓመቱን አጠናቆ ወደሶስተኛው እየተንደረደረ ይገኛል ።

ባለፈው 28-ዓመት የወያኔ ጎጠኛ አመራር ያራምድ የነበረውን ስርአት የኦሮሞ ኦነጋውያን እጅግ በከፋ ሁኔታ በማጠናከር በተለይም በአማራው ላይ የሚያደርስው በደልና ግፍ ዐይን ያወጣና ይሉኝታ የሌለው ከስግብግብነቱና ካልጠግብ ባይነቱም በላይ ፣ በጥላቻ በነቀዘ አዕምሮ አማራ በምድረ ኢትዮጵያ እንዳይኖርና ደብዛውን ለማጥፋት ግፍ በተሞላበት ግድያና ፣ ማፈናቀል የተቻለውን ሁሉ ካደረገ በኋላ ዛሬ ደግሞ በቀጥታ ወረራ የአማራው ሳልውና ለማምከን ከምን ጊዜውም በላይ እየተንደረደረ ይገኛል ።

ዛሬ በአማራው ላይ እያንዣበበ ያለው ጥቃት አይቀሬ እንደሆነ በርካታ ምሁራን ፣ የፖለቲካ ተንታኞችና አገር ወዳዶች በተደጋጋሚ ሲያሳስቡ እንደቆዩ ቢታመንም ፣ አማራው ግን ቀደም ሲል በተሰራበት የመከፋፈል ሴራ ይሁን ወይንም አማራው ፖለቲካውን በውል ያልተረዳውና ያላጤነው ስለሆነ ፣ አሊያም አማራው እራሱ ጎንደር ፣ ጎጃም ፣ ወሎ ሸዋ ብሎ በመከፋፈል ዝቅ ሲልም በየመንደሩ የማሰብ አባዜ ውስጥ ተዘፍቆ እንደሆነ ለተመልካችን ግራ በሚያጋባ ሁኔታ የመጣለት እልቂት ጎጃሜ ፣ ጎንዴሬ ፣ ጋይንቴ ፣ ደባርቄ ብሎ ነጥሎ የሚመታ የሆነ እስኪመስል ድረስ መረዳት አለመቻሉ ነው ።

አማራው መሞት የጀመረው ከ 30 ዓመት በፊት ቢሆንም ነገር ግን እነ ጀኔራል አሳምነው ፅጌና ዶ/ር አምባቸው ከተገደሉ በኋላ እንደገና አንሰራርቶ ይነሳል የሚል ግምት በብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ጎሊና ውስጥ ነበር ። እውነታው ግን ያ አልሆነም ። ይልቁንም የቁልቁለት መንገዱን እያጣደፈው ይገኛል ። ለዚህም የቁልቁለትና የውድቀት ጉዞ ምንም እንኳን የጠላት እጅ ቢኖርበትም ይልቁንም ይበልጥ ያጠናከረው በሐገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራ ያለው በኢትዮጵያዊነትም ይሁን በአማራነት ስም ተደራጅተናል የሚሉት እንደ እንጉዳይ የፈሉት ድርጅቶች እንዲ ፣ እነዚህ ድርጅቶች ሁሉም በሚባል መልኩ በየራሳቸው ከሌላው አይለው ለመንገሥ ካላቸው የተንሸዋረረ ፅኑ ምኞት የተነሳ ከሌላው የተሰወረና የማይታይ ትናንሽ ዘውድ በየኪሳቸው ይዘው በመዞራቸው ነው ቢባል ከዕውነታ የራቀ አይሆንም ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ለ30 ዓመታት በአማራው ላይ በደረሰው በደልና ሰቆቃ ምክንያት ብቻ አማራው ከማንም በላይ እንደ ብረት ተጠናክሮ በአንድነትና በፅናት አብሮ መቆም በቻለ ነበር ። ነገር ግን የርግማን ይሆን የስግብግብነት ባልለየለት ሁኔታ ያ ሊሆን አልቻለም ፣ እንዳቸውም ምንም ሕዝባዊ ወገንተኝነት የሌላቸውና ሁሉም የስልጣን ጥመኞች እንደሆኑ የሚያመላክት ተግባር እያራመዱ ነው ብዬ በፅኑ አምናለሁ ። በአሁኑ ሰዓት አማራው እንደ ሕዝብ የመኖርና ያለመኖር ህልውናው ጥያቄ ውስጥ በገባበት ወቅት በአንድነትና በህብረት መቆም ካልቻለ ፣ እኔ ብቻ የሚል አንድ ስግብግብ ቡድን ባንድ አጋጣሚ ወደ ስልጣን ቢመጣ ከወያኔም ሆነ ከኦነጋውያን የተለየ ባህሪ ይኖረዋል ማለት ዘበት ነው ። በዚህ በኔነት ብቻ ባህሪው ስልጣን ላይ ወጥቶ የጦር ሰራዊቱ ፣ ደህንነቱ ፣ ፖሊሱ ፣ የሕግ መዋቅሩ ፣ ባንኩ ወዘተ በጁ በገባ ጊዜ ምን ሊሆን እንደሚችል የሮኬት ሳይንቲስት መሆንን አይጠይቅም ። ይልቁንም በዘማናችን ከተፈራረቁት አምባ ገነኖችና ጠባቦች በቂ ተሞክሮ ስለተገኘ መጨረሻቸውን መተንበይ የነብይነት ተግባር ሳይሆን የተሞክሮ ውጤት ይሆናል ማለት ነው ።

በኔ እይታ አማራው እየመጣበት ያለውን አደጋ ምን ያክል አስጊና አደገኛ እንደሆነ የተረዳ አይመስለኝም ፣ ይህንን በድፍረት እንድናገር ያበቃኝ አማራው ምንም የተለያየ ጥቃቅን ልዩነት በመሃከላቸው ቢኖርም እንኳን ፣ ሁሉም ጊዜያዊ ችግራቸውን ወደ ጎን ገፋ አድርገው በአንድነት በመቆም የጋራ ጠላት የሆነውን በጋራ ለመመከትና በቅንጅት ሊሰሩ ፈቃደኝነት አለማሳየታቸው ነው ። የመጣው አደጋ ፋኖ ፣ መኢአድ ፣ አብን ወዘተ እያለ ለይቶ የሚመታ ሳይሆን ሁሉን ሊደፈጥጥ መምጣቱን አለመገንዘባቸው እጅግ አስገርሞኛል ። ይህንን የምለው እኔ ሳንሆን ድርጅት ነን የሚሉት እንጂ ፣ እራሳቸው አፍ አውጥተው ባይናገሩትም ባድራጎታቸውና በተግባራቸው እየመሰከሩት ስለሆነ ።

ላለፉት 28 ዓመታት የወያኔ ትግሬዎች የአማራውን ድንበር በመጋፋት እጅግ በጣም ለም የሆነውን ወልቃይትንና ራያን ወደ ትግራይ አካሎ ከዚያ በሚያገኘው ሀብት ተደላድሎ መኖርን ስለለመደ አለ አግባብ የወሰደውን የአማራ ርስት መልሶ ላለመስጠት እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ለመፋለም በቁርጠኝነት ተነስተዋል ። ለዚህም ፍልሚያ ይረዳቸው ዘንድ አስቀድመው ለብዙ ዓመታት ከዘረፉት መሬት ላይ አማራውን በማሳደድ ፣ ገሚሱን በመግደል የሕዝቡን ስብጥር በተቻለው መጠን በአድ ብሄር ብቻ ለመተካት አሌ የማይባል ጥረት አድርገዋል ፣ አማራውን ለማዳከምና ለመምታት ዛሬም ከምን ጊዜውም በላይ ይበልጥ እየሰሩ እንደሆነ ገሃድ የሆነ ያደባባይ ሚስጥር ነው ። በተመሳሳይ ሁኔታም የኦሮሞው ኦነጋዊ ቡድን በሰሜን ሸዋ ፣ በወሎ ፣ አዲስ አበባን ጨምሮ ተመሳሳይ የመሬት ዘረፋና ወረራ ላይ ተሳማርቶ ትውልደ አማራውን እያፈናቀለ ኦሮሚያ የሚላትን ተምኔታዊ ሐገር ለመገንባት እጅግ እየተጣደፈ እንደሆነ እየታየ ነው ። የትላንትናዎቹ ወያኔዎችም ሆኑ የዛሬው ተረኛ ኦነጋውያንም በተቀናጀ ሁኔታ አማራውን ማዳከም ብቻ ሳይሆን በጦር ኃይልም ለመምታት መዘጋጀታቸው ሳያንስ ይባስ ብለው ከባዕድ ሐገር ሱዳን ጋር ግንባር በመፍጠር አማራው ሊያፈገፍግበት በማይችልበት ሁኔታ በባዕዳኑም ጭምር ለማስመታት የሱዳን ወታደሮችን እያስገቡ እንደሆነ ታውቋል ።

በቀደመው የወያኔ አገዛዝ ከጎረቤት ሐገር የተደራጀ ተቀናቃኝ እንዳይነሳበት ሰፊና ለም የሆነውን የአማራን መሬት ለሱዳን መንሥት መስጠቱ ይታወቃል ። ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ በኦነጉ አብይ አሕመድ በድብቅ ከሱዳን መንግሥት ጋር ባደረገው ስምምነት የተነሳ የሱዳን የጦር ሰራዊት በጎደር ውስጥ እንጅባራ ድረስ ዘልቆ በመግባትና እንዲሁም ጓንግ በመባል የሚታወቀውን ወንዝ ተሻግሮ ምሽግ ቆፍሮ ለጦርነት እየተዘጋጀ እንደሆነ ካካባቢው ነዋሪዎች ዜናው በሰፊው እየተነገረ ይገኛል ። እንግዲህ ወያኔም ፣ ኦነግም ፣ ሱዳኑም (ድርቡሹም) ሁሉም የያቅሙን ከአማራው ርስት ላይ የለም መሬት ድርሻውን ስላገኘ ያንን ላለማጣት በአንድነት አማራውን ቢቻል ከምድረ ገፅ ማጥፋት ባይቻል ቁጥሩን እጅግ በመቀነስና ላንዴም ለሁሌም እንደማያንሰራራ አድርጎ መምታት በሚለው መርህ ሁሉም ከስምምነት እንደደረሱ ተግባራቸው ምስክር እየሆነ ይገኛል ።

ይታያችሁ ይህን የመሰለ እጅግ አስፈሪ ሁኔታ አማራው ላይ በተጋረጠበት ወቅት ደግሞ አማራ ነን የሚሉ በርካታ ድርጅቶች እንደ አሸን ፈልተው ፣ እርስ በርስ እየተናቆሩ ፣ አንዱ አንዱን እያጣጣለና እያንኳሰሰ ፣ ለጠላታቸው ተደራቢ ኃይል ሆነው ያገለግላሉ ። በሐገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራ የሚገኙ ትውልደ አማራ ምሁራን ፣ ፖለቲከኞች ፣ አክቲቪስቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ አንድም ለአማራው ሳይበጁ በሌላ ወገን ደግሞ በስልጣን ላይ ላለው ኦነጋዊ አመራር የውስጥ አርበኛ ሆነው በማገልገል ፣ ለሆዳቸውና ምናባቸው ለሳለው ሆኖም ግን መቼም ለማይጨብጡት ሽርፍራፊ ስልጣን በመቋመጥ ፣ አማራው የግፉና የስቃይ ሰለባ እንዲሆን ባንድም በሌላም የጠላት ተቀጥላ ስውር እጅ ሆነው እያገለገሉ ነው ብዬ አምናለሁ ።

በዓለማችን ታሪክ እንደሚታወቀው ባብዛኛው በሚባል ሁኔታ ወደ ስልጣን የሚመጣው የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል ነው ። በተመሳሳይ ሁኔታም ባብዛኛው ጊዜ ሕዝባዊ አመፅንና ትግልን የሚያደናቅፈው ይሄው የተማረው ክፍል ነው ። ምክንያቱም ምሁሩ በተፈጥሮው አድር ባይ ፈሪና የስልጣን ጥመኝነት ተጠቂ በመሆኑ እንደሆነም ይታመናል ። ነገር ግን ምሁሩ ወደ ስልጣን እንዲመጣ ከፍተኛውን መስዋትነትና ትግል የሚያራምደው ግን ሰፊው ሰርቶ አደር ፣ አርሶ አደር ፣ ተማሪው ፣ አስተማሪው ፣ ሾፌሩ ወዘተ እንደሆኑ ማንም የማይክደው ሃቅ ሆኖ ሳለ ፣ ለምን ምሁራን ተብዬዎች በወገናቸው እንዲህ ያለ አስተዛዛቢ የሆነ ደባ እንደሚፈፅሙ ግን ሊገባኝ አልቻለም ። በመሆኑም በምሁራን ተብዬዎቹ እጅግ ማዘኔንን ሳልገልፅ ባልፍ የታሪክ ተወቃሾች ስለሚያደርገኝ አሁንም ደግሜ ደጋግሜ በተለይ በአሁኑ ሰዓት በአስጊ ሁኔታ ላይ ያለውን የአማራ ሕዝብ የሰፈነውን ውጥረትና ስጋት ከግንዛቤ በማስገባት የአማራ ምሁራን ወደ ህሊናቸው ተመልሰው ሳይማር ላስተማራቸው ወገናቸው ወደሆነው ከአማራው ሕዝብ ጎን በህብረትና በአንድነት እንዲቆሙ ጥሪዬን በመደጋገም ባለመሰልቸት አቀርባለሁ ።

ብዙ አድር ባይ (apologists) አማራ ነን ባዮች በወገናቸው ላይ ፊታቸውን እንዳዞሩና ተንበርካኪ እንደሆኑ አይተናል ፣ ተገንዝቤያለሁም ፣ ሰሞኑንም አንድ ሆዱ የገዛው አድር ባይ በሚዲያ ቀርቦ ለጠ/ሚኒስትሩ ያለውን ተገዢነትና አጎብዳጅነት ሲገልፅ እንዲህ ብሏል ። “ጠ/ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ሲሉ እንባቸው ይቀራል” ። ጉዳዩ “ውሻ በበላበት ይጮሀል” ቢሆንም የጠ/ሚኒስትሩ እንባ የቀረረው ለኢትዮጵያ ካላቸው ፍቅር ሳይሆን ኢትዮጵያ አደረሰችብኝ ከሚሉት በደል እንዳልሆነ በምን አወቀ? ተናጋሪው ሰዎች ምን እንደሚያስቡ አውቃለሁ ብሎ ስላልነገረን ጥያቄዬ አግባብነት ይኖረዋል ። የኛም አባቶቻችን ጣሊያን የሚለውን ስም ሲያነሱ በደሉና ግፉ ስለሚታወሳቸው እንባቸው ሲቀር አይቻለሁና ።

*ጠ/ሚኒስትሩ በኢንሳ የስለላ መዋቅር ውስጥ በነበሩበት ወቅት ኦነግን በስለላ ይረዱ እንደነበር በራሳቸው አንደበት ስለነገሩን በተግባራቸው እየጠራሁ ፣ የኦነጉ ጠ/ሚኒስትር በፓስተርነት ሞያ ለዘመናት የኖሩና ፣ በሰበካ የሰለጠኑ በመሆናቸው የሚናገሯቸው ሁሉም ማለት ባይቻልም ባብዛኛው አማላይና አዘናጊ እንደሆኑ ባለፉት ሁለት ዓመታት ተፈትነው ታይተውበታል ። ከሚናገሯቸው መልካም ቃላት ውስጥ ግን አንዳችም ምድር ላይ ጠብ የሚል እውነታ የሌላቸው ይልቁንም በየመድረኩ ከሚናገሩት በተቃራኒው በመተግበር የተዋጣላቸው አጭበርባሪ ናቸው ቢባል አባባሉ ከዕውነት የራቀ አይሆንም ።*

*ሁላችንም እንደምናውቀው የኦነጉ አብይ ቀኝ እጅ የሆነው ለማ መገርሳ ከሱማሌ የተፈናቀሉ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ኦሮሞዎችን የአዲስ አበባን አሰፋፈር(demography) ለመቀየር በአዲስ አበባ አካባቢ አምጥቶ እንዳሰፈረ በድፍረት ነግሮናል ። ይህ በንዲህ እንዳለ ደግሞ የመንግሥት ስልታዊ እገዛ ባለበትና በተቀነባበረ መልኩ ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎችም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ትውልደ አማራ ግማሹ ተገድሎ ፣ ግማሹ ተዘርፎ ፣ የቀረው እየተወገረ ለዘመናት ከኖረበትና ከከበደበት ቀዬው እየተፈናቀለ አለውድ በግዴታ ወደ አማራው ክልል እንዲሄድ ተደርጓል ።*

*አሁንም በዓለማችን የተከሰተውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ተገን በማድረግ በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ ትውልደ አማራ የሆኑ የቀን ሰራተኞችን በአምስት ትላልቅ አውቶቡሶች እየተጫኑ ወደ አማራው ክልል ባሕርዳር እንዳመጧቸውና እንደበተኗቸው ሰምተናል ፣ ይህ ሲሆን ግን ሆድ አደሩና ሙቱ በአዴን/ኦዴፖ/የአማራው ብልፅግና ፣ ተባበረ እንጂ ተቃውሞውን አላሰማም ። ይህ አይነት በደልና ግፍ የሚፈፀመው በአማራና በአማራ ተወላጆች ላይ ብቻ ነው ። ተመሳሳይ ድርጊት በትግራይ ፣ በሱማሌ ፣ በኦሮሞ ወዘተ ሲፈፀም አናይም ። የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ታፍሰው ወደ ወለጋ ፣ ጅማ ፣ ባሌ ተጋዙ የሚል ሳይሆን የምንሰማው ፣ ከወለጋ ከባሌ ፣ ከአሩሲ ፣ ከጅማ ወደ አዲስ አበባ አግዘው የሃሰት መታወቂያ ማደላቸውን ነው ። የዚህ አይነቱ አካሄድ ደግሞ ልክ የቀደመው የትግሬው ወያኔ በወልቃይትና ራያ የማኅበረሰቡን አሰፋፈር(demography)ለመቀየር የተጠቀመት ስልት ሲሆን ዛሬም ተረኛው የኦነጉ የኬኛ ስርዐት በተመሳሳይ ሁኔታ ከላይ ለማ መገርሳ በነገረን መሰረት የአዲስ አበባን አሰፋፈር(demography)ለመቀየርና* ***“ፊንፊኔ”*** *ኬኛን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰሩበት ተራ ስልት እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አያደርገውም ።*

*እነ ዶ/ር አምባቸውንና ጀኔራል አሳምነው ፅጌን በጭካኔ ተገድለው ፣ የአማራ ልዩ ኃይልን በትነው ፣ የጦሩን የምዕራብ ዕዝ ከአማራ ክልል እንዲነሳ ተደርጎ ወደ ወለጋ ቀይሮ ፣ የአማራውን የተራረፈች ልዩ ኃይልና የፖሊስ ሰራዊት ትጥቅ ፈተህ ወደ ካምፕ ግባ ብሎ ፣ ኦሮሚያ ከሚለው ክልል የቻለውን ያክል ትውልደ አማራ ገድሎ ፣ አፈናቅሎ ፣ ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ ከአዲስ አበባ ትውልደ አማራን እያፈናቀለ ፣ ኦነግ ሸኔ የተባለ ሽፍታ አደራጅቶ የአማራ ወጣቶችን እያሳገተ ፣ እየገደለ ፣ ባንክ እያዘረፈ ፣ በአክቲቪስት ስም በኦነጋውያን ጃዋሮች በመቶዎች እያስገደሎ ፣ አፈናቅሎ ፣ ኦነግ እሽሩሩ እያለ ያለ መንግሥት ፣ አንድ የአማራ ገበሬ ታጠቀ ብሎ ጦር ማዝመት ፣ ከውጭ አገር መንግሥትና ከትግሬው ወያኔ ጋር አብሮ አማራን በሶስት አቅጣጫ ከቦ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲልና ፣ ከ 30 ዙር ጊዜ በላይ ፣ ከ150,000 ሺህ በላይ የኦሮሞ ልዩ ኃይል አደራጅቶ ያስቀመጠው ፣ የግድግዳ ላይ ጌጥ ሊያደርጋቸው ነው ብሎ ማሰብ ሲበዛ የዋህነት ይሆናል ።*

***“ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል”*** *የሚለው የአበው ዘያዊ አነጋገር ፣ ዛሬ የገፈቱ ቀማሽ የሆነውን አማራን እንጂ እኔን አይመለከትም የሚል የዋህ ይኖራል ብዬ አልገምትም ። በመሆኑም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚልንና በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምንን ሁሉ እንደሚመለከት ማወቅ ይገባል ። ስለሆነም ለጊዜው ስጋት ላይ ያለው አማራው ስለሆነና ባብዛኛው ትውልደ አማራን ያማከለ ማሳሰቢያ ቢሆንም ባጠቃላይ ግን ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ የሚመለከት ጉዳይ ስለሆነ ዛሬ ሁሉም ከአማራው ጎን በመቆም የጠባቦችንና የአምባገነኖችን ጥቃት በጋራ የመመከት ታሪካዊ ግዴታ አለበትና ፣ ይህንን ግዴታችንን አላንዳች ማወላወል ልንወጣ ግድ ይላል ። ታሪክም መዝገቧን ዘርግታ ትጠብቀናለችና የታሪክ ተወቃሾች አንሁን ፣ አደራ እላለሁ ።*

*ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ!*

*ድል ለአማራው ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ተጋድሎ!*

*ታዛቢው*

*April 17, 2020*